# የኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴ በጀርመን

Komitee zur Unterstützung der EPRP in Deutschland

Support Committee for EPRP in Germany

Postfach 1310 65782 Hattersheim Deutschland


---

## <u>በግንቦት 6 ቀን 2003 ዓ.ም. በፍራንክፈርት ከተማ የተጠራው ሕዝባዊ ስብሰባ በተሳካ ሁናቴ ተጠናቀቀ!!</u>

ግንቦት 8 ቀን 2003 ዓ.ም.

ይህ በጀርመን የኢሕአፓ ሀገራዊ ፓርቲ ኮሚቴና የኢሕአፓ ደጋፊ ኮሚቴ በጀርመን በጋራ የተጠራው ስብሰባ በርካታ ኢትዮጵያዊያን በተለይም ከተገኙት ተካፋዮች መካከል ብዙሃኑ ወጣት ሴቶች የሆኑበት ሕዝባዊ ስብሰባ በተሳካ ሁናቴ ተጠናቀቀ።



ስብሰባው የተከፈተው ለኢትዮጵያ ህዝብ ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶቹ እንዲከበሩ፡ የዜጎቿ አንድነት በእኩልነት እንዲረጋገጥ፡ የሕግ የበላይነት እንዲሰፍንና መልካም አስተዳደር እንዲረጋገጥ፡ ለሰላም፡ ለልማትና የኤኮኖሚ እድገት እንዲገኝ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢ ሲታገሉ ለተሰዉ ዜጎቻችን የአንድ ደቂቃ የህሊና ፀሎት በማድረግ ነበር። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በወያኔ ሰብአዊ መብታቸው ተገፎ በተለያዩ እስር ቤቶችና ማጎሪያዎች ለእስር የተዳረጉ በርካታ የፖለቲካ እስረኞች ጽናቱን እንዲሰጣቸው ኢሕአፓ ልባዊ ምኞቱን በማቅረብ፡ ከቅርብ ዘመዶቻቸው ጋር በመሆንም እስከሚፈቱ ድረስ በፅናት የሚታገልላቸው መሆኑንና ይህንንም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ የሚጋሩት ሃሳብ መሆኑን በመግለፅ ጭምርም ነበር። በመቀጠል የተጋብዙት እንግዶች ወ/ሮ ገነት ግርማ „በኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ውስጥ ሴቶች ስላላቸው ሚና“፡ አቶ ዩሱፍ ያሲን „የብሄር ጥያቄ ትላንትና ዛሬና አብሮ የመኖር ቀመር“ ና አቶ ኢያሱ አለማየሁ „በሕዝባዊ ትግል ውስጥ የድርጅትና የመደራጅት አስፈላጊነት“ በተሰኙት ርዕሶች ላይ ትምህርታዊ የሆኑና በርካታ ግንዛቤዎች የሚያስጨብጡ ሰፋ ያሉ የመወያያ ሃስቦችን ተራ በተራ አቅርበዋል።





የስብሰባው ተካፋዮችም በተሰጡት የመንደርደሪያ ሀሳቦች ላይ በመመርኮዝ ጥያቄዎችና አስተያየቶችን አቅርበው ከመድረኩም ለቀረቡት ጥያቄዎችም ሆነ አስተያየቶች ሰፋ ያሉ መልሶች ተሰጥተዋል። በውይይቶቹ መካከልም ቀስቃሽ የሆኑ ግጥሞች ተነበዋል። ታዳሚዎቹ በቀረቡላቸው ሀተታዎችና ትንተናዎች ከልባቸው የረኩ ከመሆናቸው ሌላ በርዕሶቹ ላይ በበለጠ የሚያስቡባቸው መሆናቸውንም ገልፀዋል። ለዚህም የተገኘው ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ስብሰባው ከተደመደመ በኋላ በይበልጥ ግልፅ እንዲሆንላቸው ባሰቡት ርዕስ ላይ ከእንግዶቹ ጋር ግላዊ ውይይቶች መካሄዳቸው በውይይቱ የተሰጡት ገለፃዎች፡ ትንተናዎችና አስተያየቶች በጣም አስፈላጊና ወቅታዊ በተደጋጋሚ መቅረብ የሚኖርባቸው መሆናቸውን የሚያጠናክርና የሚጠቁም እንደሆነ አሳይቷል።







ከአዘጋጆቹ በኩል ይህ አይነት ሕዝባዊ ስብሰባ በሌሎች የጀርመን ከተሞችና እንዲሁም በተለያዩ የአውሮፓ ከተሞች ለማድረግ እቅድ እንዳለ ተገልጿል። በመጨረሻም ትምህርታዊ ገለፃ ለመስጠት ጥሪያቸውን አክብረው ለተገኙት ሶስቱ የክብር እንግዶች በአዘጋጆቹና ታዳሚዎች ሥም ልባዊ ምስጋና በማቅረብ ስብሰባው ተጠናቋል። የአቶ ዩሱፍ ያሲን ፅሁፍ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ለንባብ በድረ ገፆች የሚቀርብ ይሆናል።

ለአመፅ እንነሳ!!
እናቸንፋለን!!